## ልጃችሁ በረከት ነዉ።

እግዝአብሄር የአልቢኒዝም (ሻሾነት) ተፈጥሮ ያለዉ ልጅ ሰጥቷቹሃል። እግዝአብሄር ባርካችኋል።

## ልጃችሁ ልዩ እንጂ ህመምተኛ አይደለም።

ልጃችሁ አልታመም። ልጃችሁ በቀላሉ አልቢኒዝም (ሻሾነት) የሚባል ተፈጥሮ አለዉ። በበሽታ አምጪ ተዋህሳን ወይም በቫይረስ የሚመጣ አይደለም። ከበሽታ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም። ልጃችሁ ይህን ነጭ ቆዳ የያዘዉ ከሰዉ ተላልፎበት አይደለም፤ ከልጃችሁም ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም።

ልጃችሁን መንካት (መዳበስ) ወይም በአቅራብያው መሆን ምንም አይነት አደጋ አያመጣም። ማቀፍም ሆነ ማዘል ጉዳት አያስከትልም። ልጃችሁ ህጻን ከሆነ ያለ ምንም ችግር ጡት ማጥባት ይችላሉ። ልጃችሁ በሽተኛ (ህመምተኛ) አይደለም።

## ልጃችሁ በረከት እንጂ እርግማን አደለም

አልቢኒዝም (ሻሾነት) በመናፍስት ወይም አማልክት አማካኝነት አይደለም የሚመጣው። ከእርግማን የተነሳ አይመጣም እንዲሁም ይህን ተፈጥሮ የያዘ ልጅ መውለድ እርግማን አይደለም። ልጅ ምንጊዜም ቢሆን የእግዝአብሄር በረከት ነው። እንዲህ አይነት ልጅ መውለድ በቤተሰባችሁ ላይ መጥፎ ነገር ይፈጠራል ማለት አይደለም። ችግር በተፈጠረም ጊዜ የችግሮች ሁሉ መንስኤ ልጃችሁ ነው ማለት አይደለም። ልጅ ምንጊዜም ቢሆን የእግዝአብሄር በረከት ነው።

አልቢኒዝም (ሻሾነት)ባል ለሚስት ወይም ሚስት ለባል ካለመታመን የሚመጣ አይደለም። ይህ የሁለታችሁም ልጅ ነው፤ የሁለታችሁም ልዩ፣ የተወደደ ልጅ፣ ከእግዝአብሄር የመጣ በረከት ነው። ልጃችሁ በረከት ነው፤ ነገር ግን ለየት ያሉ ተግዳሮቶች በህይወቱ ይገጥሙታል። የወላጅ ፍቅር፣ ተቀባይነት እና ድጋፍ ያስፈልገዋል። በእርገጥኝነት የእርስዎ ፍቅር እና ድጋፍ ያስፈልገዋል።

## ለምን ልጅዎ አልቢኖ (ሻሾ)ሆነ

እግዝአብሄር ነገሮች ልዩነት ሲኖራቸው ይወዳል። እግዝአብሄር የተለያየ የቆዳ ቀለም ያላቸዉን ልዩ ልዩ ሰዎችን ፈጥሯል። ሁሉንም ደሞ ይወዳቸዋል። እግዝአብሄር እናንተንም ሰርቷቹሃል። ይሄንም ልጅ እግዝአብሄር በእናቱ ማህፀን አስቦ አስቀምጦታል። እግዝአብሄር እናንተንም ልጃችሁንም ይወዳል። አልቢኒዝም (ሻሾነት)በዘር የሚመጣ ተፈጥሮ ነዉ። ይሄም ማለት ከእናት እና አባቱ የወረሰው ነው ማለት ነው። ነገር ግን ነገሮች ሁሉ በእግዝአብሄር ቁጥጥር ስር መሆናቸውን እናውቃለን። እርሱ አበቦች ሁሉ አንድ አይነት መልክ እንዲኖራቸው አይፈልግም። በዚች ምድር ላይ እርሱ የፈጠራቸው ልዩ ልዩ ቀለማት ያስደስቱን የለ? ህጻናትም እንዲሁ የተለያየ ቀለማት እንዲኖራቸው ይፈልጋል። አንዱ ቀለም ከሌላው ቀለም አይበልጥም አያንስም፤ ሁሉንም እግዝአብሄር ስለፈጠረ።

**ለምን አንዳንዶች ይፈራሉ**

አንድ አንድ ሰዎች አልቢኒዝም (ሻሾነት)ምን እንደሆነ ካለመረዳት የተነሳ ልጅዎ አቅራቢያ መሆን ሊፈሩ ይችላሉ። ብዝውን ጊዜ ሰዎች ያልተረዱት ነገር ያስፈራቸዋል። ልጅዎ በሽተኛ ነዉ ብለው ስለሚያስቡ ወደ እነርሱ እንዳይጋባባቸው ይፈራሉ። ይህ ግን ልክ አይደለም።

ልጃችሁ የተረገመ ነው ብለው ሊያስቡ ስለሚችሉም ይፈራሉ። ይህም ግን ልክ አይደለም። እግዝአብሄር ልጃችሁን ይወደዋል። ልጃችሁ የእግዝአብሄር በረከት ነው።

ከሌሎች ልጆች ልጃችሁ በቆዳው መልክ ሊለይ ይችላል፤ ነገር ግን በሌላ በብዙ መንገድ ከሌሎቹ ጋር አንድ ነው።

**ልጃችሁ መልካም ህይወት መኖር ይችላል**

ብዙ የአልቢኒዝም (ሻሾነት) ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች አድገው ታላላቅ ነገሮችን እያረጉ ይገኛሉ። አንድአንድ ታዋቂ ሙዚቀኞች፣ የመንግስት ባለስልጣናት እንዲሁም የንግድ ሰዎች የአልቢኖ(ሻሾ) ተፈጥሮ ያላቸው ናቸው። በእግዝአብሄር እርዳታ ልጃችሁ ሌሎች ልጆች ሊያረጉ የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ ይችላል።

ብዙ ይህ ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ብልህ እና አስተዋይ ናቸው። ልክ እንደማንኛዉም ሰው ነገሮችን መረዳት (መማር) ይችላሉ። ትምህርት ቤት መሄድ ይችላሉ። በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት ሊያመጡ ይችላሉ። አንድአንድ የአልቢኒዝም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ልጆች የአይናቸው ማየት ችሎታ ደካማ ሊሆን ይችላል። ልጃችሁ በትምህርቱ እየተቸገረ ከሆነ ክፍል ውስጥ የጥቁር ሰሌዳውን በደንብ መመልከት ይችል እንደሆነ ይህን አረጋግጡ። መጽሀፍቶቹንም በደንብ መምልከት መቻሉን አረጋግጡ። ክፍል ውስጥ በተሻለ ማየት እንዲቻለው ልጃችሁ የክፍል መቀመጫ ቦታውን መቀየር ይችል እንደሆነ መምህሩን አስፈቅዱ።

አልቢኒዝም (ሻሾነት)ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች እንደማንኛውም ሰው ለረዥም አመታት መኖር ይችላሉ። ይህ እንዳይሆን ሊያረግ የሚችል ብቸኛው ችግር የቆዳ ካንሰር (የቆዳ ነቀርሳ)ነው። ስለዚህም ደሞ ትንሽ ቆየት ብለን እንወያያለን።

**አልቢኖ (ሻሾ)ልጅ ሊገጥሙት የሚችሉ ሁለት ትላልቅ ችግሮች እንዴት መፍታት (መቋቋም)ይችላል**

የአልቢኒዝም (ሻሾነት) ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ሁለት ችግሮች ይገጥሟቸዋል። እናንተ ደግሞ እነዚህን ችግሮች ለልጅዎ ለማቅለል ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች አሉ።

**አንድ፤** የልጅዎ የአይን ብሌኖች ከጸሃይ የሚከላከልላቸው ጥቁር ቀለም (ሜላኒን) የለውም

የልጅዎ አይኖች የጸሃይ ብርሃን መቋቋም አይችሉም፣ ስለዚህም በቀላሉ ሊጎዱ ይችላሉ። ልጅዎ ቀን ቀን ውጭ በሚሆንበት ግዜ ሁሌ የጸሃይ መነጽር በማድረግ አይኖቹን ከጸሃይ ብርሃን ሊንከባከብ ይችላል። በተጨማሪም የጸሃይ መከላከያ ከፊፍ (ጠርዝ)ያለዉ ኮፍያ በማድረግ ለአይኖቹ ጥላ ማድረግ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወዱ ክርስቲያኖች ለልጅዎ የሚሆን የጸሃይ መነጸር ስጦታ ልከዋል። እነዚህ መነጽሮች የልጆን አይን ለመንከባከብ ይረዳሉ ብለን ተስፋ እናረጋለን። ይህን ስጦታ የምንሰጣችሁ እግዝአብሄር ለእናንተ እና ለልጃችሁ እንደሚያስብ እንድታዪ ነው። እግዝአብሄር ልጃችሁ ጥሩ ህይወት እንዲኖረው እና ለዘላለም የእርሱ ጓደኛ እንዲሆን ይሻል።

የልጅዎ የማየት አቅም ደካማ ሊሆን ይችላል። ልጅዎ በትምህርት ቤት ማየት እየተቸገረ ከሆነ መምህሩን ልጅዎ ወደፊት ቀረብ ብሎ መቀመጥ ይችል እንደሆነ ይጠይቁ። ይህን ለመጠየቅ ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ ኤቭሪ ቻይልድ ሚኒስትሪስ (ኢሲኤም)ለዚህ ሚሆን ደብዳቤ ሊያቀርብላችሁ ይችላል።

**ሁለት፡** እናንተ ከዚህ በፊት አስተውላችሁት እንደሚሆነው የልጃችሁ ቆዳ የጸሃይ ጨረረን መቋቋም ስለማይችል በቀላሉ ይጎዳል። ቆዳዉ እና ከንፈሮቹ በቀላሉ ይቆስላሉ። ብዙ የአልቢኖ (ሻሾ) ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ቆዳቸው የጸሃይ ጨረረን መቋቋም ስለማይችል ለቁስል እንዲሁም ለቆዳ ካንሰር (ለቆዳ ነቀርሳ) የተጋለጡ ናቸው።

የልጅዎ ቆዳን ከጸሃይ ለመከላከል ብዙ ነገሮች ማረግ ይችላሉ። በመጀመሪያ ልጅዎ ከጠዋቱ አራት ሰአት እስከ ቀኑ አስር ሰአት ባለው ጊዜ ዉስጥ በተቻለ መጠን ብዙ ወደ ውጭ እንዳይወጣ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ ጊዜ ላይ የጸሃይ ጨረር በጣም ሞቃታማ እና በቀጥታ የልጆን ቆዳ በከፍተኛ ሁኔታ ሊጎዳ ይችላል። በተቻለ መጠን በነዚህ ሰአታት ውስጥ ልጅዎ ቤት ውስጥ ወይም ጥላ ስር መቆየት አለበት። ከቤት ውጭ የሚሰሩ ስራዎች በጠዋት ወይም ወደ አመሻሹ የጸሃይ ኃይል በሚቀንስበት ወቅት መስራት አለባቸው።

የልጅዎን ቆዳ ረጅም እጄታ ያላቸውን ልብሶች እንዲለብስ በማድረግ መንከባከብ ይቻላል። ነጭ ወይም ነጣ ያለ ቀለም ያላቸው ከጥጥ የተሰሩ ሸሚዞች (ልብሶች)፣ እንዲሁም ረጅም ሱሪ ወይም ቀሚስ የልጆን ቆዳ ከጸሃይ ይጠልላሉ እንዲሁም የጸሃይ ጨረርን ወደ ቆዳው እንዳይደርስ አንጸባርቀው ይመልሳሉ። ልጅዎ ሸሚዙን ሙሉ በሙሉ እንዲቆልፍ ይመከራል። ፊቱን፣ አይኖቹን እና ጆሮውን ከጸሃይ ለመከላከል ሰፊ ኮፍያ ማድረገም ይችላል። በተጨማሪም የጸሃይ መከላከያ የቆዳ ቅባት መቀባት ይችላል። ይህ በልብስ ሊሸፈኑ የማይችሉ አካላትን ለመንከባከብ ይረዳል። ልጅዎ የጆሮውን ውጫዊ ክፍል እና አፍንጫውን መቀባቱን ያረጋግጡ። የጸሃይ መከላከያ ቅባቱን አይኖቹ ውስጥ በፍጹም መቀባት የለበትም። የኮኮነት ፍሬ ዘይት ከጸሃይ ጨረር አይከላከልም፤ ነገር ግን ለልጅዎ ቆዳ ጥሩ ሲሆን ጸሃይ ሊያደርስ ከሚችላቸው ጉዳቶች ሊከላከል ይችላል። ፀሃይ በልጅዎ ቆዳ ላይ የሚያደርሳቸውን አንድ አንድ ጉዳቶችን ለማስታመም እና ለማዳንም ያገለግላል። የልጅዎን ቆዳ ቆዳ ማታ ማታ ወይም ቤት ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ በኮኮነት ዘይት ማሸት ይችላሉ።

ልጅዎ የሰውነት ማጎልመሻ ክፍለ ጊዜ ላይ እንዳይሳተፍ የመመምህሩን ፈቃድ ጠይቁ። አብዛኛውን ጊዜ የሰውነት ማጎልምሻ ትምህርት ቀኑ ሞቃታማ በሆነበት ሰአት እንዲሁም ተማሪዎች ቆዳቸውን ለፀሃይ


ኢሜይል: ecmafrica@ecmafrica.org

ሚያጋለጡ ልብሶች ለብሰው የሚካሄድ ነው። ኤቭሪ ቻይልድ ሚኒስትሪስ (ኢሲኤም)ይህን የእናንተን ጥያቄ የሚደግፍ ደብዳቤ ሊያቀርብ ይችላል። ልጅዎ በክፍል ውስጥ ወይም ጥላማ ቦታ ላይ የሰውነት እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላል።

## እግዝአብሄር እናንተንም ልጃችሁንም ይወዳል

ሁልጊዜ እግዝአብሄር እናንተንም ልጃችሁንም እንደሚወድ አስታውሱ። ልጃችሁ ከእርሱ ዘንድ የመጣ ልዩ በረከት ነው። እናንተ እንዲሁም አልቢኖ (ሻሾ)ልጃችሁ ለእግዝአብሄር አስፈላጊ ናችሁ። ልጃችሁ ልክ ባለበት ሁኔታ እግዝአብሄር ይወደዋል። ልጃችሁ ለቤተሰቡ እና ለአለም በረከት መሆን ይችላል።

## ልጃችሁን ከፌዘኞች (አሿፊዎች)ጠብቁት

አልቢኒዝም (ሻሾነት)ያልገባቸዉ ሰዎች እናንተ ወይም ልጃችሁ ላይ ሊያሾፉ ይችላሉ። ክፉ እና ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን ሊናገሩ ይችላሉ። የሚናገሯቸውን ነገሮችም እውነት ናቸው ብለው ሊያምኑም ይችላሉ። በነዚህ ጊዜያት ልጃችሁን ልትንከባከቡት ይገባል። ሰዎች በሚያሾፉበት ጊዜ ልትከራከሩለትም ይገባል። አንድ ልጅ የሰዎችን ሹፈት ብቻዉን ሊቋቋም አይችልም። ሹፈት (ፌዝ) ልጅ ለእራሱ ያለዉ አስተሳሰብ ላይ ከፍተኛ እና ዘላቂነት ያለው ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።

## ልጃችሁን አበረታቱት፤ ልጃችሁ ትልቅ በረከት ነው

አንድአንድ ግድ የለሽ ሰዎች ስለአልቢኒዝም (ሻሾነት)ምንም ስለማያዉቁ ልጃችሁ እርግማን ነዉ ሊሉ ይችላሉ። ልጃችሁን ደግማችሁ ደግማችሁ በረከት እንደሆነ ልትነግሩት ያስፈልጋል። የሚፈለግ፣ የተወደደ፣ ተቀባይነት ያለው ልጅ ነው። ይህን ማድረግ ሌላ ማድረግ ከምትችሉት ነገር በላይ በህይወቱ ስኬታማ እንዲሆን ይረዳዋል።

## ተጨማሪ ጥያቄዎች አሏችሁ?

አሁን ስለተናገርነው ወይም ስለልጅዎ አልቢኖ (ሻሾ) መሆን ምን ተጨማሪ ጥያቄ አሎት?

ልጅዎ አልቢኖ (ሻሾ)በመሆኑ ምን አይነት ችግሮች ገጥመውታል?

ቤተሰብዎ አልቢኖ (ሻሾ)ልጅ በማሳደግ ዙሪያ ምን አይነት ፈተናዎች ገጥመውታል?

Every Child Ministries Uganda
PO BOX 28080
Kampala, Uganda

www.ecmafrica.org
Email: ecmafrica@ecmafrica.org

**በይበልጥ ለማስረዳት የተዘጋጀ። ይህን ማስረጃ ወላጆች የተማሩ ከሆኑ እና ተጨማሪ ማብራሪያ ከጠየቁ ብቻ ይጠቀሙ**

**አልቢኖ ልጅ ህመምተኛ ካልሆነ ታድያ ለምን ቆዳዉ ነጭ ሆነ?**

ይህ ክስተት የሚፈጠረው እንደሚከተለው ነው።

በእናት ማህፀን ውስጥ እንቁላል ይገኛል። በየወሩ አንድ እንቁላል በሴቷ ዉስጥ ይሰራል።

አባት ደግሞ የዘር ፍሬ በውስጡ አለው። ይህ የዘር ፍሬ ያለማቋረጥ ይመረታል። የወንዱ የዘር ፈሳሽ እና የሴቷ እንቁላል ልጅ ለመስራት የሚያስፈልጉ ዘር ናቸው። ሁለቱ አንድ ላይ ሲዋሃዱ አዲስ ልጅ ይፈጠራል።

ምንም እንኳ የወንድ የዘር ፈሳሽ እና የሴት እንቁላል ጥቃቅን ቢሆኑም በውስጣቸው አስፈላጊ መረጃ ይዘዋል። ይህ መረጃ ምን አይነት ልጅ እንደሚወለድ ይወስናል። ይህን መረጃ የሚወለደው ልጅ ከእናቱ ግማሽ ከአባቱ ደግሞ ግማሽ በመውሰድ በአጠቃላይ ለእድገቱ የሚያስፈልገውን ሙሉ የዘር መረጃ ያገኛል።

ይህ የዘር መረጃ የሚወለደው ልጅ ወንድ ይሁን ሴት፣ ትልቅ ይሁን ትንሽ፣ ሉጫ ወይ ከርዳዳ ጸጉር እንደሚኖረው ይወስናል። ቆዳው ምን እንደሚመስል፤ አይኖቹ ምን እንደሚመስሉም ይወስናል። ልጁ በእናቱ ሆድ ውስጥ ማደግ ሲጀምር ይህ የዘር መረጃ እንዴት ማደግ እንዳለበት ይወስናል።

አንድአንድ ሰዎች በዉስጣቸው የሚያድገውን ህፃን በጣም ጥቁር ቆዳ እንዲሰራ የሚያዝ የዘር መረጃ ይዘዋል። ሰውነት ይህን ማረግ ሚችለው በጣም ብዙ ሜላኒን በማምረት ነው። ሜላኒን ለቆዳችን ቀለም የሚሰጠው ንጥረነገር ሲሆን በተጨማሪም ቆዳችንን ከፀሃይ ይከላከላል። ነጮችም (ፈረንጆችም)ሜላኒን አላቸው፤ ነገር ግን ጥቁር ሰዎች በይበልጥ ይህ ንጥረነገር አላቸው። ስለዚህም አብዛኞች አፍሪካኖች በውስጣቸው ለሚወልዱት ልጅ ብዙ ሜላኒን እንዲሰራ የሚነግር የዘር መረጃ ይዘዋል ማለት ነው።

አንድአንድ ሰዎች ደግሞ የሚወልዱትን ልጅ "ሜላኒን አታምርት፣ ጥቁር ቆዳ አትስራ" የሚል የዘር መረጃ ይዘዋል። በዚህን ጊዜ የሚወለደው ልጅ እንደማንኛውም ልጅ ያድጋል፤ ነገር ግን ሜላኒን ወይም የቆዳ

ቀለም አይኖረውም። ሲወለድ ከቆዳው በታች ያለውን ደም ማየት ስለሚቻል ልጁ ሮዛማ ቀለም ይኖረዋል።

በዚህ መልኩ ነው ልጅዎ አልቢኖ (ሻሾ)ሊሆን የበቃው። አልቢኒዝም (ሻሾነት)በዘር የሚመጣ ክስተት ነው። በሽታ አይደለም። ከእናት እና አባት በተወረሰ ዘር የሚመጣ ተፈጥሮ ነው።